50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
የቪክቶሪያ ስትሪት እና የሆላንድ ኮርት
ፍሌሚንግተን

ውድ ነዋሪ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታልቁ የቤቶች ግንባታ (Big Housing Build) እድገት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር ለማሳወቅ እየጻፍንልዎት ነው።

አሁን ፣ የሚቀጥለው ደረጃ በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 መንደሮች ወይ ሳበርቦች ለሚኖሩ የአሁኑ እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ የሆኑ ቤቶች ወደ ማቅረቡ እያመራን ነው።

የዛሬው ማስታወቂያ በሰፈርዎ ያሉ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል እና ከእነዚህ ነዋሪዎች ጋር በመደበኛነት እንገናኛለን። **በቤትዎ ወይም በህንጻዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።**

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ ስለዚህ ቀጣይ ደረጃ በእነዚህ ሕንፃዎች ውስጥ ካሉ ነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፡-

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፕራሃን
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028፣ ወደ ተስማሚ ቤት እንዲዛወሩ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## በአቅራቢያዎ አዳዲስ ቤቶችን እየገነባን ነው

የእነዚህን ነዋሪዎች የመዛወር አማራጮችን ለመደገፍ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች በአቅራቢያው በግንባታ ላይ ናቸው። በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ኤሴክስ ስትሪት፣ ፕራሃን
- ባራክ ቢኮን፣ ፖርት ሜልበርን
- ሲሞንስ ስትሪት፣ ሳውዝ ያራ
- ሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን

እነዚህ ቤቶች ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ቀላል ይሆናሉ፣ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች የበለጠ ምቹ ይሆናሉ፣ ደህንነትን፣ ብርሃን እና አየር ማናፈሻን ተሻሽሏል እንዲሁም በረንዳዎች እና የግል የልብስ ማጠቢያዎች ይኖራቸዋል።

## በሰፈራችሁ

በ12 ሆላንድ ኮርት እና በ120 ሬስኮርስ ሮድ ላይ የቀሩ ጥቂት አባወራዎችን ዝውውራቸውን እንዲያጠናቅቁ እየደገፍን ነው። ማፍረስ ለመጀመር እየተዘጋጀን ሳለ፣ ለአዳዲስ ቤቶች ዲዛይን የማህበረሰቡን ግብአት ለማካተት እያሰብን ነው። ራዕዩ በጥሩ ሁኔታ በተነደፈ እና በደንብ በተገናኘ ሰፈር ውስጥ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች መገንባት ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአዲሱ የሆላንድ ኮርት ግንባታ ውስጥ አዳዲስ ቤቶች እና የማህበረሰብ መገልገያዎች በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እናም በቅርቡ የአዲሱ 5000 ካሬ ሜትር ማዕከላዊ ፓርክ ንድፎችን እናካፍላችኋለን።

## ስለ መልሶ ማልማት ፕሮግራም

የሜልበርን የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ዘመናዊ የምቾት፣ የተደራሽነት እና የኃይል (ኢነርጂ) ቆጣቢነት ደረጃዎችን በሚያሟሉ አዳዲስ ቤቶች ይተካሉ። እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና በማልማት ነዋሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ምቹ እና አሁን እና ወደፊት ለፍላጎታቸው ተስማሚ በሆኑ ቤቶች ውስጥ መኖር እንደሚችሉ እያረጋገጥን ነው።

## ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስዎ ከኛ ጋር መገናኘትዎ አያቋርጡ

ቤትዎ የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች መልሶ ማልማት ፕሮግራም አካል አይደለም፣ ነገር ግን በአካባቢዎ ውስጥ ለውጦች ሲከሰቱ ሊያስተውሉ ይችላሉ። በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ ከእርስዎ ጋር መገናኘታችን አናቋርጥም።

እንዲሁም በአቅራቢያዎ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማየት እና የቅርብ ጊዜ ዜናዎችን እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመቀበል ለመመዝገብ homes.vic.gov.au ድህረ ገጻችንን መጎብኘት ይችላሉ።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026